የፌዴራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር

አዋጅ ቁጥር .../2012

የጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብት በተሻለ ሁኔታ ማስከበር፣ ጥራቱን የጠበቀና የተደራጀ የጥብቅና አገልግሎት አቅርቦት መኖር፣ እና የጥብቅና አግልግሎት የሥነ-ምግባር ደረጃን ማሳደግ የሕግ የበላይነትና ፍትህ የማግኘት መብትን ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የህዝብ ጥቅምን በማስጠበቅና ፍትህን በማስፈን ዙርያ የተደራጀ፤ የመንግስትና

የሙያተኞችን ተዋጽኦ ያማከለ የጋራ አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት የሙያ ነጻነቱ የተጠበቀ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤ የጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቀጣይነትና ድርጅታዊ ዋስትና ያለው የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል የጥብቅና ድርጅት የሚመራበትንና የሚተዳደርበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤ ጠበቆች በተከታታይ ሥልጠና አማካኝነት በየጊዜው ከሚወጡ አዳዲስ ህጎች፣ የህግ ጽንሰ-ሀሳቦች እና አገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ተሞክሮዎች ጋር የሚተዋወቁበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤ በጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር የሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትን ፍትህዊ ሥርዓት መደንገግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፩ /፩/ መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የፌዴራል ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር /2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃለ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1) “ጠበቃ” ማለት የግል የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት በዚህ አዋጅ መሠረት ፍቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡

2) “የጥብቅና ድርጅት” ማለት የሕግ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡

3) “የጥብቅና አገልግሎት” ማለት የገንዘብ ክፍያ በመቀበል ወይም ወደፊት የሚገኝ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ወይም ያለክፍያ በጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅት ሊሰጥ የሚችል ማንኛውም የሕግ አገልግሎት ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ/ በሕግ ጉዳዮች ላይ ምክር መስጠት፤

ለ/ የሕግ ሰነድ ማርቀቅ ወይም በደንበኛው ስም ሰነድን ማቅረብ፤

ሐ/ በፍርድ ቤቶች፣ አስተዳደራዊ ጉባዔዎች፣ ፍርድ ቤት አከል ተቋማት፤

ለግልግል ዳኝነት ጉባዔዎች እና በሌሎች አማራጭ የሙግት መፍቻ መድረኮች ደንበኛን ወክሎ መቅረብ እና መከራከር

መ/ የተለየ ፍቃድ የሚያስፈልገው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሰነድን ማረጋገጥ፡፡

4) “ማኅበር” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 57 መሠረት የተቋቋመ የኢትዮጵያ የፌዴራል ጠበቆች ማኅበር ነው፡፡

5) “ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ” ማለት በአዋጅ ቁጥር 943/2008 መሰረት የተቋቋመው የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ነው፡፡

6) “ደንበኛ” ማለት የጥብቅና አገልግሎት ተቀባይ ሰው ነው፡፡

7) “የሥነ ምግባር ደንብ” ማለት የጠበቆች ስነ-ምግባርን አስመልክቶ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣ ደንብ ነው፡፡

8) “ስልጠና” ማለት በዚህ አዋጅ መስረት በማህበሩ አማካኝነት ለጠበቆች በስራ ላይ እያሉ የሚሰጥ ተከታታይ የህግ ስልጠና ነዉ፡፡

9) “ተቋም” ማለት ተከታታይ የህግ ስልጠና የሚሰጥ ድርጅት ነዉ፡፡

10) “ሕገ መንግስት” ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ነው፡፡

11) “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 ላይ የተመለከቱት ክልሎች ናቸው፡፡
12) “ቦርድ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 70(1) መሠረት የተቋቋመ የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ ነው፡፡

13) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰዉ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

14) በዚህ አንቀጽ በወንድ ጾታ የተደነገገው አነጋገር የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በዚህ አዋጅ መሠረት የጥብቅና ፍቃድ በሚሰጣቸው ጠበቆች ወይም የጥበቅና ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

ስለ ፍቃድ አሰጣጥ፤ ምዝገባ እና እድሳት

ንዑስ ክፍል አንድ

ስለ ፍቃድ አሰጣጥ

4. የጥብቅና ፍቃድ መርሆዎች

1) ማንኛዉም ሰዉ ፍቃድ ሳይኖረዉ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አይችልም፤ 2) የጥብቅና ፍቃድ ቋሚ ሥራ ላለው ሰው አይሰጥም፤

3) ማንኛዉም የጥብቅና ፍቃድ ማግኘት የሚፈልግ ሰዉ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፤ 4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ ማንም ሰዉ በጾታ፤ በሀይማኖት፤ በዘር ወይም በማህበራዊ አመጣጡ፤በፖለቲካ አመለካከቱ፤ በንብረቱ፤ በትዉልዱ፤ በአካል ጉዳት ወይም ማንኛዉንም ተመሳሳይ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ፍቃድ አይከለከልም፡፡

5. ፍቃድ የማያስፈልግበት ሁኔታ

የሚከተሉት አካላት የጥብቅና ፍቃድ ሳያስፈልጋቸዉ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡-

ሀ) ስለራሱ ጉዳይ የሚከራከር፤

ለ) ያለከፍያ ለትዳር ጓደኛዉ፤ ለወላጁ፤ ለልጁ፤ለአያቱ፤ለእህቱ፤ለወንድሙ፤ እነዲሁም ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ለሆነለት ሰዉ የሚከራከር፤

ሐ) ከስራዉ ጋር በተያያዘ ጉዳይ የሚከራከር ዐቃቤ ህግ፤

መ) ሕጋዊ ሰውነት ባለው የንግድ ድርጅት፣ የሰቪል ማህበረሰብ ድርጅት፤ ሕዝባዊ ድርጅት፣ የሃይማኖት ተቋም፣ የሙያ ማህበር፣ አለም አቀፍ ድርጅት ወይም በሌላ አግባብነት ባለዉ ህግ መሰረት በተቋቋመ ድርጅት ተቀጥሮ የተወከለ ሰው፡፡
ሠ) የመንግስት መስርያ ቤትን ወይም የልማት ድርጅትን በሚመለከት የሚከራከር ማንኛዉም የመንግስት መስርያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ባለስልጣን ወይም ሀላፊ ወይም በእርሱ የተወከለ ሰዉ፤

ረ) ማንኛዉም የሰራተኛ ማህበር መሪ ወይም ማህበሩ የሚወክለዉ ሰዉ

6. ፍቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1) ማንኛዉም በጥብቅና ሙያ መሰማራት የሚፈልግ ሰዉ የጥብቅና ፍቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ዜግነት ያለዉ ወይም ትዉልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ፤

ለ) ዕውቅና ካለዉ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ቢያንስ በህግ የመጀመርያ ዲግሪ ያለዉ፤

ሐ) ለመጨረሻ ጊዜ ይሰራበት ከነበረበት ተቋም ድርጅቱን ከመልቀቁ በፊት ባሉት ሁለት አመታት ዉስጥ በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ እና የመልካም ስነምግባር ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፤

መ) በዚህ አዋጅ በተቀመጠዉ መስፈርት መሰረት የሙያ ሀላፊነት መድህን ዋስትና የገባ፤ እና

ሠ) በህግ ሙያ የሚፈለገዉን የስራ ልምድ ያሟላ እና እንደአስፈላጊነቱ ፍቃድ ለማግኘት የሚሰጠዉን የሙያ መግቢያ ፈተና ያለፈ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው አስፈላጊ ሰነዶችን በማያያዝ የጥብቅና ፍቃድ ማመልከቻውን ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) መሰረት የሚቀርበዉ የፈተና ውጤት ዋጋ የሚኖረዉ ውጤቱ በታወቀ በአንድ አመት ጊዜ ዉስጥ ከቀረበ ብቻ ነዉ፡፡

7. ፍቃድ የማያሰጡ ምክንያቶች

ማንኛዉም ሰዉ የጥብቅና ፍቃድ የማይሰጠው፡-

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች ያላሟላ ከሆነ፤

2) ታስቦ በሚፈፀምና ሶስት ዓመትና ከዚያ በላይ ጽኑ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል
ተከሶ ጥፋተኛ ከተባለ እና አግባብነት ባለው ህግ ያልተሰየመ ከሆነ፤

3) በሕግ አገለግሎት እንዳይሰማራ በሕግ ወይም በፍርድ ቤት የተከለከለ፤

8. የዉጭ ሀገር ጠበቆች

1) በውጭ ሀገር ሕግ መሰረት የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ ያለው ጠበቃ በያዘው የውጭ ሀገር ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ በኢትዮጵያ ውስጥ ለደንበኞቹ ጊዜያዊ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት የሚችለው፡-

ሀ) ፍቃድ የሰጠው የውጭ ሃገር ሕግን በሚመለከት ሲሆን፤ እና
ለ) በዚህ አዋጅ መሰረት የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት ፍቃድ ካገኘ ጠበቃ ጋር በመሆን ብቻ ነው።

2) በዚህ አዋጅ መሰረት የተደነገጉ የጥብቅና ፍቃድ የማያሰጡ፣ የሚያሰርዙ ወይም የሥነ ምግባርና ሌሎች ግዴታዎች እንደአግባብነታቸው ለአጭር ጊዜ የጥብቅና አገልግሎት በሚሰጡ የውጭ ሃገር ጠበቆችም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

9. ፍቃድ ስለመስጠት

1) በዚህ አዋጅ መሰረት የፌዴራል የጥብቅና ፍቃድ የሚሰጠዉ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ነዉ፤

2) አመልካቹ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6(2) መሰረት የተሟላ ማመልከቻ ባቀረበ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ተገቢ የሚለዉን ዉሳኔ መስጠት አለበት፤

3) የጥብቅና ፍቃድ ማመልከቻ ተቀባይነት ካላገኘ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘበትን ምክንያት ለአመልካቹ በ10 የስራ ቀናት ዉስጥ ማሳወቅ አለበት፤

4) ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ፍቃድ እንዲሰጥ ከወሰነ በ15 የስራ ቀናት ዉስጥ የጥብቅና ፍቃዱን ለአመልካቹ መስጠት አለበት፤

5) የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ በሚሰጥበት ጊዜ በፍቃድ ደብተር ላይ መጠቀስ ያለባቸዉ ነጥቦች ዝርዝር ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

6) ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማመልከቻዉን ዉድቅ ካደረገዉ አመልካቹ ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን ካወቀበት ጊዜ አንስቶ በ15 የስራ ቀናት ዉስጥ ቅሬታዉን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፤

7) ቦርዱ የጠቅላይ ዐቃቤ ህግን ዉሳኔ ካጸናው አመልካቹ ውሳኔውን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

10. ቃለ መሀላ ስለማስፈጸም

የቃለ መሀላ ፈጻሚዉን ዕምነት ለማስተናገድ ሊደረጉ የሚችሉ ምክንያታዊ ለውጦች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛዉም የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ የሚሰጠዉ ጠበቃ የሚከተለዉን ቃለ መሀላ በጽሁፍ ያረጋግጣል፡

«እኔ ዛሬ ቀን ዓ.ም የፌደራል የጥብቅና ፈቃድ ስቀበል የሀገሪቱን ህገ-መንግስት እና ህጎች ላከብር እና ላስከብር፤ ለፍትህ ስርዐቱ ተልዕኮ መሳካት በመልካም ስነ-ምግባር በሙያዬ በቅንነት እና በታማኝነት በመስራት የምወክላቸዉን ደንበኞቼን ጥቅም ህግ በሚፈቅደዉ አግባብ ላስከብር፤ ከተከራካሪዎቼ እና ሙያ ባልደረቦቼ ጋር በመግባባት እና በመከባበር ልሰራ እና፤
ባለኝ እዉቀት እና ችሎታ ለህግ የበላይነት ተገቢዉን ዕገዛ ለማድረግ ቃል እገባለሁ»

11. የጥብቅና ፍቃድ አይነቶች

የጥብቅና ፈቃድ ዓይነቶች፡-

1) የፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፍቃድ፤

2) የፌደራል ማናቸዉም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፍቃድ፤ እና

3) የፌደራል ልዩ ጥብቅና ፍቃድ ናቸዉ።

12. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥብቅና ፍቃድ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥበቅና ፍቃድ ይሰጠዋል፡-

1) ዕውቅና ካለዉ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሕግ የመጀመርያ ዲግሪ የተመረቀ እና በህግ ሙያ ቢያንስ ሶስት ዓመት ልምድ ያለው፤

2) ለደረጃው የሚሰጠውን የጥበቅና ፈቃድ መግቢያ ፈተና ያለፈ፤

3) የሙያ ኃላፊነት የመድኅን ዋስትና መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ ያቀረበ፤

4) ለመጨረሻ ጊዜ ይሰራበት ከነበረበት ተቋም ድርጅቱን ከለቀቀበት ጊዜ በፊት ባሉት ሁለት አመታት ዉስጥ በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ እና መልካም ስነምግባር ያለዉ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፡፡

13. የፌዴራል ማናቸውም ፍርድ ቤት ጥበቅና ፈቃድ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ

ኢትዮጵያዊ የፌዴራል ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥበቅና ፈቃድ ይሰጠዋል፡-

1) ዕውቅና ካለዉ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሕግ ትምህርት የመጀመርያ ዲግሪ ያለዉ እና በህግ ሙያ ቢያንስ የአምስት ዓመት ልምድ ያለው፤

2) እንደ አስፈላጊነቱ ለደረጃው የሚሰጠውን የጥበቅና ፍቃድ መግቢያ ፈተና ያለፈ፤

3) የሙያ የኃላፊነት የመድኅን ዋስትና መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ ያቀረበ፤

4) ለመጨረሻ ጊዜ ይሰራበት ከነበረበት ተቋም ድርጅቱን ከለቀቀበት ጊዜ በፊት ባሉት ሁለት አመታት ዉስጥ በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ እና መልካም ስነምግባር ያለዉ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፡፡

14. ልዩ የጥበቅና ፍቃድ

1) ልዩ የጥበቅና ፍቃድ፡-

ሀ) የህብረተሰቡን አጠቃላይ መብት እና ጥቅም ለማስከበር በነጻ አገልግሎት ለሚሰጥ ሰዉ ወይም ድርጅት፤ ወይም

ለ) አቅም ለሌላቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የህግ ድጋፍ አገልግሎት ለሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ህግ ትምህርት ቤቶች እና የህግ መምህራን ሊሰጥ ይችላል፡፡

2) ማንኛዉም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) መሰረት ልዩ የጥበቅና ፍቃድ ማግኘት የሚፈልግ ሰዉ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) በህግ ዕዉቅና ካገኘ የትምህርት ተቋም የመጀመርያ ዲግሪ ያለዉ እና በሙያዉ ቢያንስ 5 አመት ያገለገለ፤

ለ) ከሚወከለዉ የህብረተሰብ ክፍል ወይም ደንበኛ ክፍያ የማይቀበል፤ እና

ሐ) ምግባረ ብልሹነትን በሚያመለክት ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ፡፡

3) ማንኛውም የጥበቅና ፍቃድ ያለዉ ጠበቃ ልዩ የጥበቅና ፍቃድ ሳያስፈልገዉ የልዩ ጥበቅና አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህን አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡ ፡

4) ልዩ የጥበቅና ፍቃድ የተሰጠዉ ሰዉ ወይም ድርጅት የጥበቅና አገልግሎቱን ሲሰጥ ይህን አዋጅ እና የጠበቃ ስነምግባር ደንብን በተከተለ መልኩ መፈጸም አለበት፡፡

15. ለሕግ መምህራን ፍቃድ ስለመስጠት

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4(2)፣ 6(1)(ሐ)፣ 12(4) እና 13(4) ስር የተደነገገዉ ቢኖርም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሕግ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምር ማንኛዉም የሕግ መምህር በአንቀጽ 12 እና 13 ላይ የተጠቀሰዉን ካሟላ የጥበቅና ፍቃድ ሊሰጠዉ ይችላል፤
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የጥበቅና ፍቃድ እንዲሰጠው የሚያመለክት የሕግ ትምህርት ቤት መምህር የጥበቅና ሥራው የመማር ማስተማር ሂደቱን የማያስተጓጉል መሆን አለበት፡፡

16. ስለ ጥበቅና ሙያ መግቢያ ፈተና

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6(1) ስር የተደነገጉትን የሚያሟላ ማንኛዉም በጥበቅና አገልግሎት መሰማራት የሚፈልግ ሰዉ የጥበቅና ሙያ መግቢያ ፈተና መዉሰድ ይኖርበታል፡፡

2) በኢትዮጵያ በሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ በህግ መምህርነት ለሰባት ዓመት ያገለገለ፤ በዳኝነት፣ በዐቃቤ ሕግነት፣ በመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት በህግ አማካሪነት እና በነገረ ፈጅነት ቢያንስ ለአምስት ዓመት ያገለገለ፣ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት፣ በሀይማኖት ተቋማት፣ በአለም አቀፍ ድርጅቶች፣ በንግድ ድርጅቶችና ሌሎች ተቋማት በህግ አማካሪነት እና በነገረ ፈጅነት ቢያንስ ለለሰባት ዓመት ያገለገለ ሰው ሥራውን በለቀቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የጥበቅና ፍቃድ ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ የጥበቅና ፍቃድ ያለፈተና ሊሰጠው ይችላል፤

3) ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፡-

ሀ) ከጠበቆች ማህበር እና ሌሎች አግባብነት ካላቸዉ አካላት ጋር በመሆን ፈተናዉን ቢያንስ በአመት 2 ጊዜ የማዘጋጀት፤

ለ) የፈተናዉን ስነ-ስርዓት እና ጊዜ የመወሰን፤

ሐ) የፈተና ወረቀቶችን ማረም፤ ለማለፊያ የሚያበቃ ነጥብ መወሰን እና ዉጤት በይፋ የማሳወቅ፤ እና

መ) ፈተናዉን በስኬት ላጠናቀቀ ተፈታኝ ፈተናዉን ማለፉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት

ምዝገባ እና እድሳት

17. ምዝገባ

1) ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የጥበቅና ፍቃድ የተሰጣቸዉን ጠበቆች እና የጥበቅና ድርጅቶች ሙሉ መረጃ ዘመናዊ በሆነ መንገድ መመዝገብ አለበት፤

2) በምዝገባ ስርዓቱ ውስጥ የሚካተቱ ዝርዝር ነጥቦች ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

3) ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የመዘገባቸዉን ሰዎች ስም ዝርዝር በየሶስት ወሩ ለማህበሩ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

18. ከጠበቃ ወይም ጥበቅና ድርጅት ጋር ስለሚሰሩ ሰዎች

1) ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የህግ ጉዳይ ጸሀፊ፤ የጠበቃ ረዳት እና ሌሎች ለስራዉ የሚያስፈልጉ ሰራተኞችን ሊቀጥር ይችላል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ቅጥር የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ቅጥሩ በተፈጸመ በሁለት ወራት ዉስጥ ማሳወቅ እና ማስመዝገብ አለበት፡፡

3) ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚከተሉትን በህግ ጉዳይ ጸሀፊነት ወይም በጠበቃ ረዳትነት መቅጠር አይችልም፡-
ሀ) የጥብቅና ፍቃዱ የታገደን ወይም የተሰረዘን ሰው፤

ለ) ከመዝገብ ስሙ የተፋቀን ሰው፤

ሐ) ከመስርያ ቤቱ በዲሲፕሊን ጥፋት የተባረረን ሰው፤

መ) ከስነ-ምግባር ጋር በተያያዘ ወንጀል ተከሶ የተቀጣ እና ያልተሰየመን ሰው፤ ወይም

ሠ) ቋሚ ስራ ያለዉን፤

ረ) የሕግ ትምህርት ወይም የስራ ልምድ የሌለዉን፡፡

19. ስለፍቃድ እድሳት

1) የጥብቅና ፈቃድ በየዓመቱ ፈቃዱ ጸንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ መታደስ አለበት፤

2) ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተጠቀሰዉ ጊዜ ውስጥ ፍቃዱን ሳያሳድስ ከቀረ በሚቀጥለው አንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት የሚጣልበትን የገንዘብ ቅጣት ከፍሎ ፍቃዱ ይታደስለታል፤

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጠበቃዉ ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ፍቃዱን ያላሳደሰዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን የሚያሳይ አሳማኝ ማስረጃ ካቀረበ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት የሚጣልበትን የገንዘብ ቅጣት ከፍሎ ፍቃዱ ሊታደስለት ይችላል፤

4) ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በዚህ አንቀጽ መሰረት ፍቃዱን ያላሳደሰ እንደሆነ የዲሲፕሊን ክስ ይቀርብበታል፡፡

20. ፍቃድ ለማሳደስ የሚቀርቡ ማስረጃዎች

ማኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፍቃድ ለማሳደስ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል፡-

1) የታክስ ክሊራንስ፤

2) የፀና የመድህን ዋስትና ማስረጃ፤

3) ጠበቃዉ ለተከታታይ የህግ ስልጠና የተመደበዉን አነስተኛ የስልጠና ሰዓት ማጠናቀቁን የሚገልጽ ማስረጃ፤

4) የጠበቆች ማህበር አባል ስለመሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ፡፡

21. ፍቃድን ስለመመለስ

1) ማንኛውም ጠበቃ፡-

ሀ) ከሙያው ውጭ በሆነ ሥራ በዋናነት የተሰማራ እንደሆነ፤

ለ) በማናቸዉም ሁኔታ ሙያዊ አገልግሎት ለመስጠት ያልቻለ እንደሆነ፤

ሐ) የጥብቅና አገልግሎት ለማቆም ከወሰነ፤

የጥብቅና ፍቃዱን ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መመለስ አለበት፤
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ጠበቃዉ ፍቃድ ለመመለስ ሲያመለክት ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የጥብቅና ፍቃድ ደብተሩን ወዲያዉኑ መረከብ አለበት፡፡ ሆኖም ጠበቃዉ የጥብቅና አገልግሎቱን ማቋረጡን የሚገልጽ ማስረጃ ለጠበቃዉ የሚሰጠዉ ጠበቃዉ ከሚመለከተዉ አካል የግብር ክሊራንስ ይዞ ሲቀርብ ይሆናል፤

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ፍቃዱን የመለሰ ጠበቃ ወደ ጥብቅና ስራው መመለስ ከፈለገ ፍቃዱን መልሶ ሊወስድ ይችላል፤ ሆኖም ጠበቃው ከአገልግሎቱ ከሁለት ዓመት በላይ ተለይቶ ከቆየ ፍቃዱ የሚመለስለት ለደረጃዉ የሚሰጠውን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ወስዶ ካለፈ ብቻ ነው፡፡

ክፍል ሶስት

የጠበቆች የሙያ ግዴታ

ንዑስ ክፍል አንድ

ጠቅላላ የጠበቆች ግዴታ

22. ከጥብቅና ፍቃድ ጋር የተያያዘ ግዴታ

ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

1) በደንበኛ፣ በፍርድ ቤት ወይም በማንኛውም አግባብ ባለው አካል የጥብቅና ፍቃድን እንዲያሳይ ሲጠየቅ የማሳየት ግዴታ አለበት፤
2) የጥብቅና ፍቃዱን በማንኛውም ሁኔታ ለሌላ ሰው መጠቀሚያ ወይም መገልገያ

አሳልፎ መስጠት የለበትም፡፡

23. ስለጥብቅና አገልግሎት ውል እና ተያያዥ ግዴታ

1) ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ከደንበኛው ጋር የሚያደርገውን የጥብቅና አገልግሎት ውል በፅሑፍ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ 2) የጥብቅና አገልግሎት ዉሉ ደንበኛው ለጠበቃው የሚከፍለውን አጠቃላይ የገንዘብ ክፍያ፤ የአከፋፈሉን ስልት እና ጊዜ፤ ጠበቃዉ በጉዳዩ ላይ የሚያስገነዉን ዉጤት ዓይነት ወይም ዓይነቶች የሚያካትት ሆኖ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር ጉዳዮች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡

3) ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፤-

ሀ) ለጥብቅና አገልግሎት መስጫ የሚሆን ቢሮ የማሟላት፤
ለ) የጥብቅና ስራን በደላላ ያለመስራት፤ እና ሐ) የጥብቅና ውልን ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት ማቋረጥ እና በጥብቅና ውሉ ከተገለፀው የክፍያ መጠን በላይ ተጨማሪ ክፍያ ከደንበኛ ያለመጠየቅ ግዴታ አለበት፡፡

24. ስለታማኝነትና ለፍትህ አጋር መሆን

ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

1) የጥብቅና አገልግሎት ስራውን በታማኝነት የመስራትና ለፍትህ አጋር የመሆን ግዴታ አለበት፤

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፩) ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጠበቃ የያለበቂ ምክንያት ጉዳይን ያለማጓተት፣ ምስክሮችን በሐሰት ያለማደራጀት፣ ሀሰተኛ ማስረጃ ያለማቅረብ/ያለማስቀረብ፣ ተዘጋጅቶ የመቅረብና ተገቢውን ክርክር የማድረግ ግዴታ ያለበት ሆኖ ሌሎች መሰል ከጠበቃ ስነምግባር ጋር የተያያዙ ግዴታዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

3) ተዘጋጅቶ የመቅረብና ተገቢውን ክርክር የማድረግ፣ የህግ መሰረት የሌለውንና የማያዋጣ ጉዳይን መያዝ፣ የደንበኛውን ወይም ባለጉዳዩን ሚስጢር የመጠበቅ እና ሌሎች መሰል ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን መፈፀም የለበትም፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት

ተከታታይ የሕግ ስልጠና የመውሰድ ግዴታ

25. ዓላማ

የተከታታይ የሕግ ስልጠና ዓላማ ጠበቆች የሙያ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል ወቅታዊ ዕውቀትና ክህሎት በቀጣይነት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡

26. ስለተከታታይ የሕግ ስልጠና

1) ማንኛውም ጠበቃ በዓመት ዉስጥ በድምሩ ከአስር ቀናት ያላነሰ ተከታታይ የሕግ ስልጠና የመውሰድ ግዴታ አለበት፤

2) የህግ ስልጠናው በተከታታይ ወይም በዚያው ዓመት ውስጥ በተለያየ ጊዜ ሊሰጥ የሚችል ሆኖ በተለያየ ጊዜ የሚሰጥ የህግ ስልጠናን በተመለከተ በእያንዳንዱ ዙር የሚሰጠው ስልጠና ከሶስት ቀናት ሊያንስ አይችልም፡፡

3) በተከታታይ የሕግ ስልጠና የሚሸፈኑ የስልጠና ዘርፎችን፣ የስልጣና ጊዜውን ርዝመት፤ አጠቃላይ የስልጠና አሰጣጥ መርሃ-ግብር፤ የስልጠና ክፍያ እና ሌሎች ከስልጠና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ ማህበሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፤
4) ተከታታይ የሕግ ስልጠናው በዋናነት፡-

ሀ) ተግባር እና ንድፈ ሐሳብ ላይ ያተኮረ መሰረታዊና እና ሥነ-ሥርዓታዊ ህጎች ስልጠና፣ እና

ለ) የጠበቆች አሰራር እና የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ ስልጠናዎችን ያጠቃልላል፡፡

27. ዕውቅና ስለተሰጣቸው ተቋማት

1) ተከታታይ የህግ ስልጠና የሚሰጠው በማህበሩ እውቅና በሚሰጠው ተቋም ነው፤

2) ማህበሩ ለተቋሙ ዕዉና ከመስጠቱ በፊት የሚሰጡ የሥልጠና ዓይነቶችን ቀድሞ ማፅደቅ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም በቅድሚያ የጸደቁት የሥልጠና ዓይነቶች በማህበሩ ወደፊት ሊሻሽሉ፣ ሊታገዱ፣ ወይም ሊሠረዙ ይችላሉ፤

3) የተከታታይ የሕግ ስልጠና ሰጪዎች ዕውቅና የሚያገኙበት ሥነ ሥርዓት እና

መሥፈርቶች በተመለከተ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

28. ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት

1) የስልጠና ተቋሙ በስልጠና ላይ ያሉትን ሰልጣኞች ስልጠና ከጀመሩበት እንዲሁም ስልጠና ያጠናቀቁ ሰልጣኞችን ስልጠናውን ከጠናቀቁበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ለማህበሩ ማሳወቅ አለበት፤ 2) አንድ ጠበቃ ማህበሩ ባሳወቀው የስልጠና ጊዜ ለመሰልጠን የማያስችል በቂ ምክንያት ካለው ምክንያቱን ለማህበሩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

29. የተከታታይ የሕግ ስልጠና አለመከታተል

1) አንድ ጠበቃ በዚህ ንዑስ ክፍል የተቀመጡትን የተከታታይ የሕግ ስልጠና ግዴታዎች ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ ማህበሩ ይህንኑ ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

2) ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ከተከታታይ የስልጠና ግዴታ ጋር ተያይዘው ያለበቂ ምክንያት የስልጠና ግዴታውን ለመውሰድ ፈቃደኛ ያልሆነ ጠበቃ የድሲፕሊን ክስ ሊመሰርትበት ይችላል።

30. ተከታታይ የህግ ስልጠና ግዴታን ስለማራዘም

1) ማንኛውም ጠበቃ በአሳማኝ ምክንያት ማህበሩ በሚያወጣው የስልጠና ጊዜ ውስጥ የስልጠና ግዴታውን መውሰድ ካልቻለ ጠበቃው ስልጠናውን ማህበሩ ባወጣው ጊዜ ውስጥ መውሰድ ስላለመቻሉና የስልጠና ጊዜው እንዲራዘምለት ማህበሩ ከያዘው የስልጠና ጊዜ ከአንድ ወር በፊት ቀድሞ ለማህበሩ በማመልከቻ ማሳወቅ አለበት።

2) ጠበቃዉ የስልጠና ጊዜዉ እንዲራዘምለት የሚያቀርበዉ ማመልከቻ ስልጠናዉን መዉሰድ እንዳይችል ያደረገውን ምክንያት፣ ስልጠናዉን ለመዉሰድ ያደረገውን ጥረት፤ እና በቀጣይ መቼና በምን አግባብ እንደሚወስድ ያለውን ዕቅድ የሚገልጽ መሆን አለበት።
3) ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የቀረበለት ማመልከቻ አሳማኝ ሆኖ ካገኘው የስልጠና ጊዜውን በዚያው ዓመት ውስጥ ጠበቃው በጠየቀው ጊዜ ወይም እራሱ በመሰለው ጊዜ ሊቀይርለት ይችላል። ማህበሩ ጥያቄዉን ከተቀበለዉ የቅያሪውን ሁኔታ ወይም ጥያቄውን ካልተቀበለው ያልተቀበለው መሆኑን በ15 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለጠበቃው ማሳወቅ አለበት።

4) ጠበቃው በዓመት መውሰድ የሚጠበቅበትን የህግ ስልጠና ግዴታ በዚያው ዓመት አጠቃሎ ካልቻለና ስልጠናዉን ያልወሰደዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ ማስረጃ ካቀረበና ማህበሩ ካመነበት ጠበቃው ያልወሰደውን የስልጠና ጊዜ ወደ ቀጣይ ዓመት በማሸጋገር በቀጣይ ዓመት መውሰድ ከሚጠበቅበት የስልጠና ግዴታ ጋር ደርቦ እንዲወስድ ሊፈቅድለት ይችላል።

ንዑስ ክፍል ሶስት

ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታ

31. ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ

1) ማንኛዉም ጠበቃ በዓመት ለ.....ሰዓት ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት። አገልግሎቱ የሚሰጠዉም፦

ሀ) የመከፈል አቅም ለሌላቸዉ ሰዎች፤

ለ) ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች፤ ለሲቪክ ማህበራት፤ እና ለማህበረሰብ ተቋማት፤

ሐ) ፍርድ ቤት የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ ለሚጠይቅላቸዉ ሰዎች፤

መ) ሕግን፤ የህግ ሙያን እና የፍትህ ስርአቱን ለማሻሻል ለሚሰሩ ኮሚቴዎች እና ድርጅቶች

ነዉ።።

2) ማንኛውም ጠበቃ ለሕዝብ ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታውን መወጣቱን የሚገልጽ ማህደር መያዝ የሚኖርበት ሲሆን፤ ማህደሩም እያንዳንዱ አገልግሎት የተሰጠበትን ቀን፣ አይነቱን እና የወሰደውን ጊዜ የሚገልጽ መሆን አለበት።።

32. የነፃ የጥብቅና አገልግሎት የሚሰጥበትን ጉዳይ ተቀብሎ የማስተናገድ ግዴታ

1) ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ እያንዳንዱ ጠበቃ በዓመት መስጠት ከሚጠበቅበት የነፃ የጥብቅና አገልግሎት መጠን ሳያልፍ በነፃ የጥብቅና አገልግሎት ሊሰተናገዱ የሚገባቸውን ጉዳዮች እያጣራ ለጠበቆች ይመራል።።

2) እያንዳንዱ ጠበቃ በዓመት መስጠት ከሚጠበቅበት የነፃ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታ ሳያልፍ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የሚመራለትን የነፃ ጥብቅና አገልግሎት ተቀብሎ የመስራት ግዴታ አለበት።።
3) ማህበሩ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የነፃ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጥ የመራለተን ጠበቃ በዚህ አዋጅ እና በጠበቆች ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት መፈጸሙን መቆጣጠር እና መከታተል አለበት።።

ንዑስ ክፍል አራት

መድን እና የደንበኞች ንብረት

33. የሙያ ኃላፊነት መድን የመያዝ ግዴታ

1) ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ሥራውን በአግባቡ ሳይወጣ በመቅረቱ ምክንያት በደንበኛው ላይ ሊደርስ ለሚችል ጉዳት ካሳ የሚሆን የሙያ ኃላፊነት መድን መያዝ አለበት፤

2) ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ሊይዙት የሚገባውን የሙያ ኃላፊነት መድን መጠን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል።።

34. የመድን ሰጪው ግዴታዎች

1) ለጠበቃ ወይም ለጥብቅና ድርጅት የሙያ ኃላፊነት መድን የሰጠ መድን ሰጪ የመድን ውሉ ሲቋረጥ ወይም ግዴታው እንዳይፈፀም ሊያደርግ የሚችል ሁኔታ ሲፈጠር ሁኔታውን ወዲያውኑ ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማሳወቅ አለበት፤

2) መድን ሰጪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተቀመጠውን ግዴታውን ባለመወጣቱ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት።።

35. የደንበኛን ንብረት ስለማስተዳደር

ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

1) ከሙያ ሥራው ጋር በተገናኘ በይዞታው ወይም በአስተዳደሩ ሥር የሚገኝን የደንበኛው ወይም የሦስተኛ ወገንን ንብረት አስተዳደርን ጥበቃ ከራሱ ንብረት ፍጹም በማይገናኝበት ሁኔታ ለይቶ ማስተዳደር አለበት።።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱትን የደንበኛው ወይም የሶስተኛ ወገን ንበረቶች የሚመለከቱ ማናቸውም መረጃዎችና ሰነዶች ጉዳዩ ካለቀት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የመያዝ ግዴታ አለበት።።

36. የደንበኛ የአደራ ሒሳብ

1) በጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ እጅ የሚገኝ የደንበኛ ገንዘብ ከጠበቃው ወይም ከጥብቅና ድርጅቱ በተለየ ሒሣብ ወስጥ መቀመጥ አለበት፤

2) ቦርዱ ጠበቆች ወይም የጥብቅና ድርጅቶች የደንበኞች አደራ ሒሳብ ለመያዝ ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፤
3) የደንበኛው የአደራ ሂሳብ በጠበቃው ወይም በጥብቅና ድርጅቱ ማንቀሳቀስ የሚቻለው ክፍያ ሊፈፀምባቸው የሚገቡ ስራዎች መከናወናቸውን እና በደንበኛው ስም መደረግ ያለባቸው ወጪዎች በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፤

4) ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ የደንበኛ ወይም የሦስተኛ ወግ ጥቅም ያለበት ገንዘብ ወይም ሌላ ንበረት ሲቀበል ለደንበኛው ወይም ለሦስተኛ ወገን ወዲያው ማሳወቅ አበለት፤

5) በዚህ አዋጅ ከተመለከተው ወይም ከሕግ ወይም ከደንበኛው ጋር በተደረገ ስምምነት ካልተፈቀደ በስተቀር አንድ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለከፍያ ያልዋለ በአደራ ሂሳብ ውስጥ የተቀመጠን ገንዘብ ደንበኛው ወይም መብት ያለው ሶስተኛ ወገን ሲጠይቅ ወይም ጉዳዩ ሲጠናቀቅ ወዲያውኑ ከበቂና የተሟላ ሪፖርት ጋር ማስረከብ አለበት፡፡

ክፍል አራት

ስለጥብቅና ድርጅት

37. የጥብቅና ድርጅት ስለማቋቋም

በዚህ አዋጅ መሰረት የፀና የጥብቅና ፈቃድ ያላቸው ቢያንስ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ጠበቆች አንድ ላይ በመሆን የጥብቅና ድርጅት ማቋቋም ይችላሉ፡፡

38. የአገልግሎት ወሰን

1) የጥብቅና ድርጅት ዋነኛ ተግባር የጥብቅና አገልግሎት መስጠት ነው፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅት ከጥብቅና አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች አገልግሎቶች ሊሰጥ ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

39. የጥብቅና ድርጅት አደረጃጀት እና ኃላፊነት

1) የጥብቅና ድርጅት ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር አደረጃጀት ይኖረዋል፤

2) የጥብቅና ድርጅት፡-

ሀ) ውል መዋዋል፤

ለ) የንብረት ባለቤት መሆን፤

ሐ) በስሙ መክሰስና መከሰስ እና ሌሎች የህግ ሰዉነት ያለዉ ድርጅት የሚኖረዉ መብት እና ግዴታ ይኖረዋል፡፡

3) የጥብቅና ድርጅት ሽሪኮች ለሶስተኛ ወገን የሚኖርባቸው ኃፊነት በጥብቅና ድርጅቱ ውስጥ ባላቸው የመዋጮ ድርሻ ልክ የተወሰነ ይሆናል፤

4) የጥብቅና ድርጅት አባላትን የሚመለከት ለውጥ ቢመጣም የጥብቅና ድርጅት ህልውና ይቀጥላል፤

5) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 52 ስለ ግብር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት መስጠቱ በኢትዮጵያ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ሕጎች መሠረት አገልግሎቱን የንግድ ወይም የኢንቨስትመንት ሥራ አያሰኘውም፡፡

40. ስለ ጥብቅና ድርጅት ስያሜ

1) የጥብቅና ድርጅት አባላት ማንኛውንም ስያሜ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቱ መጠሪያ እንዲሆን መምረጥ እና መወሰን ይችላሉ፤

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ለጥብቅና ድርጅቱ መጠሪያነት የተመረጠው ስም በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በሚከተሉት ምክንያቶች ተቀባይነት ላይኖረዉ የሚችለዉ፡-

ሀ) ከሌላ የጸና የጥብቅና ድርጅት ስም ጋር ተመሳሳይ ከሆነ፤

ለ) ደንበኞች ድርጅቱን ከሌላ የጥብቅና ድርጅት በቀላሉ መለየት እንዳይችሉ በሚያስችል መልኩ ሊያሳስት ወይም ሊያደናግር የሚችል ከሆነ፤ እና

ሐ) ለሕግ ወይም ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ ከሆነ፡፡

3) የጥብቅና ድርጅት ስም የጥብቅና ድርጅት መሆኑን የሚያመለክትና ከስሙ በስተመጨረሻ “ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር” ወይም (“ኃ.የተ.የሽ.ማ”) የሚል ሐረግ ያለው መሆን አለበት፤

4) በጥብቅና ድርጅቱ ስም የሚወጡ ሰነዶች በሙሉ በግልጽ ስሙን እና “ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር” የሚለውን ሐረግ መያዝ አለባቸው፡፡

41. የመቋቋሚያ መሥፈርቶችና ሥነ ሥርዓቶች

1) የጥብቅና ድርጅት በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በመመዝገብ ይቋቋማል፡፡

2) የጥብቅና ድርጅት ለማቋቋም የሚከተሉት ሰነዶች ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መቅረብ አለባቸው፡-

ሀ) የሽሪኮቹን ሙሉ ስምና ፊርማ የያዘ ማመልከቻ፣

ለ) የመመሥረቻ ጽሑፍ፣

ሐ) የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ
መ) የሽሪኮቹ የጥብቅና ፈቃድ ቅጂ፣ እና

ሠ) ሽሪኮች ድርጅቱን ለመመስረት የተስማሙበትን የሽርክና ስምምነት፤ የድርጅቱን ዓላማ በአጭሩ የተገለጸበት እና በምስረታ ሂደት ድርጅቱን የሚወክለዉ ሽሪክ የተሰየመበት ቃለ-ጉባኤ፡፡

3) ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የቀረቡለት ሰነዶች ከዚህ አዋጅና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕግጋት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸዉን ካረጋገጠ ማመልከቻውን በተቀበለ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ የጥብቅና ድርጅቱን ይመዘግባል፤ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

4) ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የቀረቡለት ሰነዶች ከዚህ አዋጅና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕጎች ጋር የሚጣረሱ ናቸው ብሎ ካመነ ማመልከቻውን በተቀበለ በ 20 የሥራ ቀናት ውስጥ ውድቅ ማድረግና ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን መነሻ የሆነውን ምክንያት በመግለጽ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፤

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ያቀረበው ማመልከቻ ውድቅ የተደረገበት ቅሬታዉን በ15 የስራ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ በቦርዱ ውድቅ ከተደረገ ቅሬታዉ ውድቅ የተደረገበት ውሳኔ በተሰጠ በ15 የስራ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡

42. የመመሥረቻ ጽሑፍ

1) የጥብቅና ድርጅት የመመሥረቻ ጽሑፍ በዋናነት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ
አለበት፡-

ሀ) የሁሉንም ሽሪኮች ስም እና አድራሻ

ለ) የጥብቅና ድርጅቱን ስም፣

ሐ) የጥብቅና ድርጅቱን ዋና መሥሪያ ቤት እና ቅርንጫፍ ካለ ቅርንጫፉን/ ወይም ቅርንጫፎቹን፣

መ) የጥብቅና ድርጅቱን ዓላማ፣

ሠ) የሽሪኮችን መዋጮ ዓይነት፣ መጠን እና ዋጋቸው የተሰላበትን ዘዴ፣

ረ) የጥብቅና ድርጅቱ ትርፍና ኪሣራ ላይ የእያዳንዱን ሽሪክ ድርሻ፣

ሰ) የጥብቅና ድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የሚሾምበትን መንገድ፣ ሥልጣንና ኃላፊነቶቹን፣

ሸ) የሽርክና ማኅበሩን የቆይታ ዘመን፣

ቀ) በሕግ ወይም በሽሪኮቹ ስምምነት መሠረት በመመሥቻ ጽሑፍ ውስጥ እንዲካተቱ የተወሰኑ ሌሎች ነገሮችን፡፡

2) የዚህን አዋጅና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎችን የሚጥስ ድንጋጌ የያዘ የመመሥረቻ ጽሑፍ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

43. የመዋጮ ዓይትና መጠን

1) የጥብቅና ድርጅት ሽሪኮች ዋነኛው መዋጮ ክህሎት መሆን አለበት፤

2) ሽሪኮች መዋጮዎችን በገንዘብ ወይም በዓይነት ማዋጣት ይችላሉ፤

3) የጥብቅና ድርጅት ሸሪኮች የመዋጮ መጠን የድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት የሚበቃ
መሆን አለበት፤

4) ገንዘብ ባልሆነ ማናቸውም መንገድ በጥብቅና ድርጅት ሸሪክ የሚደረግ መዋጮ ዋጋ በሁሉም ሸሪኮች ስምምነት እና አግባብነት ባላቸው ሕግጋትና ደንቦች ይወሰናል፡፡

44. የሸሪኮች መብትና ግዴታ

1) የጥብቅና ድርጅት ሸሪክ የሚከተሉት መብቶች አሉት፡-

ሀ) በጥብቅና ድርጅቱ ስብሰባዎች የመካፈል እና ድምጽ የመስጠት፣

ለ) በድርሻው መጠን በዚህ አዋጅ ወይም በመመሥረቻ ጽሑፉ በተወሰነው መሠረት ከጥብቅና ድርጅቱ ትርፍ ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ሲከስም ከተጣራው የማኅበሩ ሐብት ከሚተርፈው ሐብት የመካፈል፤

ሐ) የጥብቅና ድርጅቱን አጠቃላይ አሰራር የመከታተል፣ የማወቅ፤

መ)በመመሥረቻ ፅሁፍ፣ በዚህ አዋጅና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተመለከቱ፣ ወይም ከሸርክና ማኅበሩ ተፈጥሮ የሚመነጩ ሌሎች መብቶችና ጥቅሞችን የመጠቀም፡፡

2) የጥብቅና ድርጅት ሸሪክ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

ሀ) ለጥብቅና ድርጅቱ መክፈል የሚጠበቅበትን መዋጮ በወቅቱ መክፈል፣

ለ) በማናቸውም ጊዜ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት በትጋት
የመሥራት፣

ሐ) ለራሱ ጥቅም የሚያስገኝ ቢሆንም ባይሆንም የጥብቅና ድርጅቱን ጥቅም ከሚጻረሩ ድርጊቶች ወይም ኃላፊነትን ከሚያጓድሉ ተግባራት መታቀብ፣ እና

መ) በዚህ አዋጅ፣ አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች፣ በመመሥረቻ ጽሑፉ የተመለከቱ ወይም ከሸርክና ማኅበሩ ተፈጥሮ የሚመነጩ ሌሎች ግዴታዎችን የመወጣት፡፡

45. ትርፍ እና ኪሣራ ክፍፍል በጥብቅና ድርጅቱ የመመሥረቻ ጽሑፍ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር የማኅበሩ ሸሪኮች የድርጅቱን ትርፍ እና ኪሳራ ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ሲከስም ከተጣራው የማኅበሩ ሐብት የሚተርፈውን ሐብት እኩል የመካፈል መብት አላቸው፡፡

46. የሸሪኮች ለውጥ

1) አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ የተጣለው ክልከላ እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅቱን ለሚለቅ ሸሪክ የድርሻው ዋጋ እና የትርፍ ድርሻው ሊከፈለው ይገባል፡፡

2) የጥብቅና ድርጅት ሸሪክ በሚሞት ጊዜ የሸሪኩ መብትና ግዴታዎች ለህጋዊ ወራሾቹ ይተላለፋሉ፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በሌሎች ሽሪኮች በግልጽ ካልተፈቀደላቸው በቀር የሽሪኩ ህጋዊ ወራሾች የጥብቅና ድርጅቱ ሽሪክ ሆነው ሊቀጥሉ አይችሉም፡፡

47. ባለቤትነት እና መዋቅር

1) በጥብቅና ድርጅት የታቀፉ የፀና ጥብቅና ፈቃድ ያላቸው ጠበቆች ቢያንስ የጥብቅና ድርጅቱ 3/4(ሦስት አራተኛ) ካፒታል ባለቤት መሆን አለባቸው፡፡

2) ጠበቃ ያልሆኑ ባለሙያዎች እስከ 1/4 (አንድ አራተኛ) የሚደርስ የጥብቅና ድርጅቱ ካፒታል ባለቤት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈጻጸም ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

3) የውጭ ሀገር ጥብቅና ፍቃድ ያላቸው ጠበቆች ወይም የጥብቅና ድርጅቶች 1⁄4(ከአንድ አራተኛ) ያልበለጠ የካፒታል ድርሻ ኖሯቸው ከሌሎች የሀገር ውስጥ ጠበቆች ጋር በመሆን የጥብቅና ድርጅት ማቋቋም ወይም የተቋቋመ ጥብቅና ድርጅት ባላድርሻ መሆን ይችላሉ፡፡

48. በጥብቅና ድርጅት ስር በሚሠሩ ጠበቆች ላይ የተጣለ ክልከላ

በጥብቅና ድርጅት ውስጥ ሽሪክ ሆኖ የሚሠራ ማንኛውም ጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅቱ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ ሠራተኛ የሽርክና ወይም የሥራ ቅጥር ዘመኑ ጸንቶ ባለበት ጊዜ በሚከተሉት ተግባራት ውስጥ መሳተፍ አይችልም፡-

1) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሌላ የጥብቅና ድርጅት ሽሪክ ወይም ሠራተኛ መሆን፣

2) በሚሠራበት የጥብቅና ድርጅት ውስጥ የተጣለበትን ግዴታ ለመወጣት አስፈላጊ መሆኑ በድርጅቱ ቀደም ብሎ ካልፈቀደ በስተቀር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሌላ የጥብቅና ድርጅትን መርዳት ወይም መተባበር፣

3) የግል የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤

4) የጥብቅና ድርጅቱ ሳያውቅና ሳይፈቅድ በራሱ ስም የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ከደንበኛ መቀበልና ለግል ጥቅም ማዋል፤
5) ማንኛውንም ከጥብቅና ድርጅቱ አላማና ተግባር ጋር የሚጣረስና የጥቅም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ስራ በግሉም ሆነ ተቀጥሮ መስራት፡፡

49. የጥብቅና ድርጅት አስተዳደር

1) የጥብቅና ድርጅት በመመሥረቻ ጽሑፍ ወይም በሽሪኮች ውሳኔ በተሾሙ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቁጥር ባላቸው ሥራ አስኪያጆች ይተዳደራል፤

2) የጥብቅና ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የሕግ ባለሙያ የሆነ ሽሪክ መሆን አለበት፤

3) የጥብቅና ድርጅት ስራ አስኪያጅ ድርጅቱን በዋናነት ያስተዳደራል፣ማንኛውንም ህጋዊ የድርጅቱን መብት ለማስጠበቅና የድርጅቱን ግዴታ ለመወጣት የጥብቅና ድርጅቱን ይወክላል፣ የድርጅቱ ተጠሪ ይሆናል፣ ድርጅቱን ወክሎ ይከሳል፣ይከስሳል፣ ይከራከራል፣ጠበቃ ወይም ሶስተኛ ወገን ይወክላል፤

4) የጥብቅና ድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የግል ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በሚፈፅመው ስህተት ምክንያት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ስራ አስኪያጁና የጥብቅና ድርጅቱ በአንድነትና በነጠላ ጎላፊ ይሆናሉ፤

5) የጥብቅና ድርጅቱ ጣምራ ሥራ አስኪያጆች በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 3 ለተገለጸው ግዴታ በአንድነት እና በተናጥል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

50. የሥራ አስኪያጅ ግዴታዎች

1) ሥራ አስኪያጁ በሕግ፣ በመመሥረቻ ጽሑፍ፣ በሽርክና ስምምነቱ፣ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መወጣት አለበት፡

2) የጥብቅና ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ድርጅቱ በመመሥረቻ ጽሑፍ፣ በውስጠ ደንቦች፣ በሽርክና ስምምነቱ፣ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መወጣቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1)እና(2) የተጠቀሰው ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ
ስራ አስኪያጁ፡-

ሀ) አጠቃላይ የጥብቅና ድርጅቱን የጥብቅና አገልግሎት አሰጣጥ እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣

ለ) በደንበኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመቀበልና በማጣራት ቅሬታው አግባብ ሆኖ ሲያገኘው ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ፣

ሐ) የድርጅቱን የስራ ክንውን ሪፖርት የማዘጋጀትና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማቅረብ፣

መ) ድርጅቱን አዲት የማስደረግና መክፈል የሚጠበቅበትን ታክስ በታክስ ህጉ መሰረት በወቅቱ የማሳወቅና የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

51. የጥብቅና ድርጅቱ ውሳኔዎች

1) በጥብቅና ድርጅቱ መመሥረቻ ጽሑፍ፣ በሽርክና ስምምነት ወይም ተፈጻሚነት ባለው ሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተሰወነ በስተቀር ቢያንስ ከግማሽ በላይ ድርሻ ያላቸዉ አባላቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

2) የጥብቅና ድርጅቱ ውሳኔዎች የሚጸድቁት ስብሰባ ላይ ከተገኙት ሽሪኮች ቢያንስ 60% ድርሻ ያላቸዉን ድምጽ ሲያገኝ ነው፡፡

52. ግብር

1) የጥብቅና ድርጅት ከሚያገኘው ገቢ ላይ የገቢ ግብር አይከፍልም፤

2) እያንዳንዱ ሽሪክ ከጥብቅና ድርጅቱ ትርፍ በሚደርሰው የትርፍ ክፍፍል ድርሻ ላይ የገቢ ግብር መክፈል አለበት፤

3) በያንዳንዱ ሽሪክ መከፈል ያለበትን ታክስ/ግብር የጥብቅና ድርጅቱ ተቀናሽ አድርጎ በመያዝ ለግብር ሰብሳቢው አካል መክፈል አለበት፡፡

53. ህልዉና እና መፍረስ

1) የጥብቅና ድርጅት ህልውና በሽሪኮቹ ሞት፣ መልቀቅ፣ ችሎታ ማጣት ወይም ሽሪኮቹን በሚያውክ ማናቸውም ለውጥ አይፈርስም፤

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊፈርስ ይችላል፡-

ሀ) የሽርክና ማኅበሩን ለማፍረስ ሽሪኮች ሲስማሙ፣

ለ) የጥብቅና ድርጅቱ መክሰሩ በፍርድ ቤት ሲታወጅ፣

ሐ) የሁሉም ሽሪኮቹ የጥብቅና ፈቃድ ሲሰረዝ፣

መ) የፀና የጥብቅና ፈቃድ ያላቸው ሽሪኮች ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ሲልና ቁጥራቸው በነደለ በስድስት ወራት ውስጥ የሽሪኮቹ ቁጥር ቢያንስ ወደ ሁለት ካላደገ፤

3) የጥብቅና ድርጅት ሲፈርስ ከመዝገብ ይሰረዛል።

4) ሃላፊነቱ የተወሰነ ድርጅትን መፍረስ የሚመለከቱ በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ድንጋጌዎች የጥብቅና ድርጅት መፍረስን በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

54. የጥብቅና ድርጅት እና ሽሪኮች ኃላፊነት

1) በሽርክና ስምምነቱ ከተፈቀደው ውጭ በያዙት ጉዳይ ላይ ያልተገባ ተግባር ካልፈፀሙ ወይም ሥራቸውን በአግባቡ ባለመወጣታቸው ወይም በማታለል ወይም አውቀው ባደረሱት ጉዳት ካልሆነ በስተቀር ከጥብቅና አገልግሎት መስጠት ጋር በተያያዘ በጠበቆችና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች አማካኝነት በደንበኞች እና ሌላ ሶስተኛ ወገኖች ላይ የሚደርስ ጉዳት በጥብቅና ድርጅቱ የደረሰ ጉዳት እንደሆነ ተቆጥሮ ድርጅቱ ሀላፊነት ይወስዳል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የጥብቅና ድርጅቱ ሀብት በሶስተኛ ወገኖች ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለመሸፈን ካልበቃ የጥብቅና ድርጅቱ ሽሪኮች ድርጅቱ ውስጥ ባላቸው ድርሻ ልክ ሃላፊነት ይኖርባቸዋል።

55. ገንዘብ ጠያቂዎች

1) የጥብቅና ድርጅቱ ገንዘብ ጠያቂዎች ከድርጅቱ ማናቸውም ሐብት ላይ ገንዘብ መጠየቅ ይችላሉ፤

2) ከጥብቅና ድርጅቱ ላይ ገንዘብ ጠያቂዎች ከሽሪኮች የግል ንብረት ላይ ገንዘብ መጠየቅ አይችሉም።

56. የጥብቅና ድርጅት ግዴታዎች

በዚህ አዋጅ እና በንግድ ህጉ ስለሃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማሕበር የተቀመጡት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጥብቅና ድርጅት የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

1) ከሽሪኮቹ የሙያ ኃላፊነት መድን በተጨማሪ የጸና የሙያ ኃላፊነት መድን መግዛትና ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ይዞ መገኘት፣

2) ተገቢውን የሒሳብ ሰነድ መያዝ፣

3) የደንበኞቹን ምሥጢር በጥብቅ መጠበቅ፣

4) በውጭ አዲተር በየዓመቱ አዲት መደረግ፣

5) ይህንን አዋጅ፣ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ሕግጋትና የሙያ ሥነ ምግባር ደንቦችን ማክበር፣ እና

6) የመመሥረቻ ጽሑፉ ላይ ማሻሻያዎች ሲያደርግ ማሻሻያው በተፈረመ በ፴ ቀናት ውስጥ ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ግልባጩን የማቅረብ።

57. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት

በዚህ አዋጅ ከሚመራዉ ጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ተፈጥሮ ጋር የማይቃረኑ እስከሆነ ድረስ የንግድ ህጉ እና አግባብነት ያላቸዉ ሌሎች ህጎች በዚህ አዋጅ በሚቋቋም የጥብቅና ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

ክፍል አምስት

የጥብቅና አገልግሎት አሰተዳደር

ንዑስ ክፍል አንድ

የፌደራል ጠበቆች ማህበር

58. *መቋቋም*

1) የኢትዮጵያ የፌዴራል ጠበቆች ማኅበር ከዚህ በኋላ “ማህበሩ” እየተባለ የሚጠራ
በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) ማኅበሩ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት አለው፤

3) ማኅበሩ ሁሉንም ፍቃድ የተሰጣቸው የፌዴራል ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች በአባልነት ያቀፈ ነው፡፡

4) ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፍቃድ ሲሰጠው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የማህበሩ አባል ይሆናል፡፡

59. ዋና *መሥሪያ* ቤት

የማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ቅርንጫፍ ቢሮዎች ሊከፍት ይችላል፡፡

60. የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤ ስለመጥራት

1) ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ይህ አዋጅ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ባለው

ጊዜ ውስጥ የማህበሩን የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ይጠራል፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተጠራው ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩን

አመራር አካላት ይሰይማል፡፡

61. ስለ በጀት

1) የማህበሩ ዋነኛ የገቢ ምንጭ ከአባላቱ የሚሰበሰብ መዋጮ ይሆናል፡፡

2) ማህበሩ ከሌሎች ህጋዊ ምንጮች የሚያገኛቸዉ ገቢዎች እንደተጠበቁ ሆኖ እራሱን እስኪችል ድረስ ከመንግስት የገንዘብ እና ሌሎች ድጋፎች ይደረጉለታል፡፡

62. የማህበሩ አቋም

1. ማኅበሩ የሚከተሉት አመራር አካላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ጠቅላላ ጉባኤ፤

ለ) ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

ሐ) ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት፤

መ) ዋና ፀሐፊ፤ እና

ሠ) ሌሎች ሰራተኞች፡፡

2. ስለ ጠቅላላ ጉባኤ ፤ ፕሬዝዳነት፤ ምክትል ፕሬዝዳንት እና ሌሎች ሰራተኞች ዝርዝሩ ማህበሩ በሚያወጣዉ ህገ-ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤

3. ማህበሩ እንደ አስፈላጊነቱ ስራዉን ለማከናወን ኮሚቴዎች ወይም በስሩ የሚሰሩ የስራ ክፍሎች ሊያደራጅ ይችላል፡፡

63. የማህበሩ ስልጣን እና ተግባራት ማህበሩ የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ተከታታይ የሕግ ስልጠናን በበላይነት ይመራል፤ የተከታታይ የህግ ስልጠናን

የሚመለከቱ የአዋጁን ድንጋጌዎች ያስፈጽማል፤ 2) የተከታታይ የሕግ ስልጠና ሰጪዎችን እውቅና ይሰጣል፤ 3) ይህንን አዋጅ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች በሚጥሱ የተከታታይ

የሕግ ስልጠና ሰጪዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤ 4) ከተከታታይ የሕግ ስልጠና ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ክፍያዎችን በተመለከተ

ረቂቅ መመሪያ ያወጣል፤ ያስፈጽማል 5) የአደራ ሂሳብ አፈጻጸምን አስመልክቶ መመሪያ አዘጋጅቶ በጠቅላላ ጉባኤዉ

ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤ 6) ማናቸውም የአደራ ሂሳብ አያያዝና አመራር በትክክል እየተካሄደ መሆኑን

ለመቆጣጠር በማናቸውም ጊዜ የኡዲት ምርመራ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፤ 7) ከአደራ ሂሳብ አያያዝ ጋር የሚነሱ የደንበኞች ቅሬታዎችን ይቀበላል፣

ማናቸውንም ሰው በማነጋገር ምርምራ ለማድረግ ይችላል፤ 8) ከአደራ ሂሳብ ጋር የተያያዘ ሥራን በአግባቡ ያለመወጣት ሁኔታ ሲከሰት ጉዳዩ በሥነ-ምግባር ጉባኤ ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኝ ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ሊመራው ይችላል፤ 9) ከአደራ ሂሳብ ከሚገኝ ወለድ ወይም ማናቸውም ገቢ አጠቃቀምን አስመልክቶ

መመሪያ ያዘጋጃል፣ በጠቅላላ ጉባኤዉ ሲጸድቅ በተግባር ያውላል፤ 10) በዚህ ዓዋጅ ሌሎች አንቀጾች ለማህበሩ የአደራ ሂሳብን አስመልክቶ የተሠጡ

ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤ 11) ስለአደራ ሂሳብ ምንነት፣ አያያዝና፣ ሪፖርት አደራረግ እንዲሁም መደረግ ስላለበቸው ጥንቃቄዎች ተገቢው ግንዛቤ እንዲፈጠር ተከታታይ ስልጠናዎችን ይሰጣል ወይም እንዲሠጡ ያደርጋል፤ 12) ሌሎች ከአደራ ሂሳብ አስተዳደር ጋር ተያይዞ ለማህበሩ የሚሠጡትን ተግባራት

ያከናውናል፤ 13) የደንበኞች ጥቅም መጠበቁን ያረጋግጣል፤እንዲሁም የደንበኞችን ጥቅም

ለማስጠበቅ ጠቀሜታ ያላቸው የጠበቃ መብቶች መከበራቸውን ይከታተላል፤ 14) የጥብቅና ሙያ እና የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት እንዲያድግ አስተዋጽዖ

ያደርጋል፤ 15) የአባላቱን መብት እና ጥቅም ያስከብራል፤ 16) የማህበሩ አባላት ይህን አዋጅና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች እና መመሪያዎችን በማክበር የጥብቅና አገልግሎትን የሚሰጡ መሆኑን ይከታተላል፡፡

64. የጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባራት

ጠቅላላ ጉባዔው በዚህ አዋጅ መሰረት ፍቃድ የተሰጣቸውን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች በሙሉ የሚያካትት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖታል፡-

1) የማህበሩን ፕሬዝደንት እና ምክትል ፕሬዝደንት ይሾማል፣ ይሽራል፤
2) የጥብቅና አገልግሎትን በተመለከተ የሕግ የህግ ጥናት በማድረግ የጥናት ውጤቱን ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

3) የማኅበሩን ስታራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያጸድቃል፤

4) የአባላትን መዋጮ መጠን ይወስናል፤

5) የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን እና የውጪ ኡዲተሮችን ሪፖርት ይመረምራል ያፀድቃል፤

6) ለአባላቱ ጠቅላላ ጥቅም እና ለፍትሕ ተደራሽነት ጠቀሜታ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ይወስናል፡፡

7) የውጭ ኡዲተሮችን ይሾማል፤

8) በሌሎች የማኅበሩ አካላት የሚሰጡ ውሣኔዎች ከሕዝብ ጥቅም እና ከማኅበሩ ዓላማ ጋር የሚጣጣሙ መሆኑን ያረጋግጣል፤

9) ለማኅበሩ ሌሎች አካላት በግልጽ ባልተሰጡ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤ እና

10) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ስልጣኑን በከፊል ለሌላ አካል በውክልና ይሰጣል፤

11) የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣ያፀድቃል፡፡

65. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቋም

1) ማኅበሩ የአስፈፃሚነት ስልጣን ያለው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

2) ሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴው ሰባት አባላት ይኖሩታል፡፡

3) የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባኤው ይመረጣሉ፡፡

66. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት

የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚከተሉተ ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ማኅበሩን ያስተዳድራል፤

2) የማኅበሩን ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔን ይጠራል፤

3) የጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔዎችን ይፈጽማል ያስፈጽማል፤

4) በጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

5) የሠራተኞችን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፤

6) የሠራተኞችን ደመወዝና አበል ይወስናል፤

7) ፕሬዝዳንቱ እና ምክትል ፕሬዝዳንቱ ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

67. የፕሬዝደንት እና ምክትል ፕሬዝደንት ስልጣንና ተግባራት

1) ፕሬዝዳንቱ አጠቃላይ የማኅበሩን ሥራ የሚመራ ሆኖ ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ይሆናል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዝዳንቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

ሀ) ማህበሩን ወክሎ ውል ይዋዋላል፣ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ ማህበሩ በሚከሰስበት፣ በሚከሰሰበት ወይም ሌላ ተመሳሳይ የህግ ጉዳይ ማህበሩን ወክሎ የሚቀርብ ጠበቃ ይወክላል፣የማህበሩን ጉዳይ ለማስፈፀም የማህበሩን ሰራተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን እንደአስፈላጊነቱ ይወክላል፤

ለ) የማኅበሩን ዓመታዊ ዕቅድ፣ በጀት፣ የሥራ ክንውን እና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤

ሐ) ለስራ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ረቂቅ ያዘጋጃል፣ በስራ አስፈፃሚው ኮሚቴው ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) በማኅበሩ የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሠረት የማኅበሩን ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሠ) የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በሚሰጠው መመሪያዎችና መሠረት የማኅበሩን ስራዎች ያሰራል፤ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ባለው ግንኙነት ማኅበሩን ይወክላል፡፡

ረ) የጠቅላላ ጉባዔና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፡፡

ሰ) በጠቅላላ ጉባዔውና በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

3) የማህበሩ ምክትል ፕሬዝዳንት፡-

ሀ) ፕሬዝዳንቱ በማይኖሩበት ጊዜ ወይም ሥራውን ሊሰራ በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

ለ) በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ወይም በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

68. ዋና ፀሐፊ

1) ዋና ፀሐፊው በስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ የሚሾም ሆኖ ተጠሪነቱ ለፕሬዝደንቱ ይሆናል፤

2) ዋና ፀሐፊው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

ሀ) የማኅበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል፣ያከናውናል፤
ለ) የጠቅላላ ጉባኤውና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ቃለ ጉባኤዎች በአግባቡ መያዛቸውንና መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ) ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመማከር የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፤

መ) ሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴ በሌላ ሁኔታ እንዲፈፀም የመወሰን ስልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ከሌሎች ሠራተኞች ጋር በመሆን የማኅበሩን የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፤ ያንቀሳቅሳል፡፡

ሠ) የማኅበሩን የንብረት አስተዳደር እና የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በአግባቡ መዘርጋቱን እና የሂሣብ ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፡፡

ሰ) የማህበሩ ንብረትና ሂሳብ ተቀባይነት ባለው የሂሳብ ዘዴ መያዙን ያረጋግጣል፡፡

ሸ) ሌሎች በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው እና በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

69. በማህበሩ ውስጠ-ደንብ ስለሚወሰኑ ጉዳዮች

የጠቅላላ ጉባኤ እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አመራር አካላት አደረጃጀት፣የስራ ድርሻ፣ የምርጫና ስብሰባ ሰነ-ስርዓት፣የማህበሩ ልዩልዩ አካላት የስራ ዘመን እና ሌሎች ለማህበሩ በህግ የተሰጡ ስልጣንና ተግባራት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ማህበሩ በሚያወጣው ውስጠ-ደንብ ይወሰናሉ፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት

የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ

70. *መቋቋም*

1) የጠበቆች ቦርድ ከዚህ በኋላ “ቦርዱ” እየተባለ የሚጠራዉ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2) ቦርዱ ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ ሰባት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከጠበቆች ማህበር ሶስት፤

ለ) ከጠቅላይ *ዐ*ቃቤ ህግ *ሁ*ለት፤

ሐ) ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ፤

መ) ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥብቅና ፍቃድ የሌላቸዉ የህግ *መ*ምህራን አንድ፡፡

3) የቦርዱ አባላት የ*ሥ*ራ ዘመን *ሦ*ስት ዓመት ሲሆን ከሁለት የ*ሥ*ራ ዘመን በላይ *መ*መረጥ አይችሉም፡፡

4) የቦርዱ ሰብሳቢ በጠቅላይ *ዐ*ቃቤ ህግ ከአባላቱ *መ*ካከል የሚሾም ሲሆን ጸሀፊው ደግሞ በአባላቱ የሚመረጥ ይሆናል፡፡

71. የቦርዱ ስልጣን እና ተግባራት

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በማኅበሩ የሚወሰዱ ዕርምጃዎችና ዉሳኔዋች፤ እንዲሁም በማህበሩ በሚወጡ *መ*መሪያዎች እና ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶች ሕጋዊነት ላይ ቁጥጥር የማድረግ፤

2) በማህበሩ የሚወሰኑ ዉሳኔዎች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ተቀበሎ *መ*መርመር እና ዉሳኔ *መ*ስጠት፤

3) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 76(4) *መ*ሰረት የዲሲፕሊን ጉባኤዉ፤ አንቀጽ 78 *መ*ሰረት የጥብቅና *ሙ*ያ *መ*ግቢያ ፈተና ኮሚቴዉ፤ እንዲሁም አንቀጽ 83(1) *መ*ሰረት ጠቅላይ *ዐ*ቃቤ ህግ በሚሰጡት ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታን ተቀብሎ ይመረምራል፤ ዉሳኔ ይሰጣል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሱት ኮሚቴዎች ወይም ተቋም ወይም ጉባኤዉ በአግባቡ ያላጣራዉ ወይም ያላጤነዉ ፍሬ ነገር ወይም ማስረጃ ካለ ይሄዉ ተጣርቶ ወይም ተገናዝቦ እንዲቀርብለት ለኮሚቴዎቹ ወይም ለጉባኤዉ ለአንድ ጊዜ ተመልሶ እንዲታይ ያደርጋል፡፡

5. ከጥብቅና አገልግሎት ጋር በተያያዘ ጥናት በማድረግ የጥናት ውጤቱን

ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡

6) የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ መጠንና የአከፋፈል ሥርዓት በመመሪያ ይወስናል፡፡

72. ስለቦርድ ጽህፈት ቤት እና በጀት

1) ቦርዱ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መስሪያ ቤት ዉስጥ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል

2) የቦርዱ ጽህፈት ቤት ሰራተኞች በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ይመደባሉ፤ ጽህፈት ቤቱ ሚሰራዉ ስራ ቦርዱ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

3) የቦርዱ አባላት የቦርዱን ስራ በሚፈፅሙበት ጊዜ ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ይሸፈናል፤

4) ስለቦርዱ በጀት አስተዳደርና ስለቦርድ አባላት ክፍያ ዝርዝሩ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

73. የቦርድ አሰራር እና ውሳኔ

1) ቦርዱ የአባላቱን መደበኛ ስራ በማይጎዳና የቦርዱን ስራ በማይስተጓጎል መልኩ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤
2) ከቦርዱ አባላት ቢያንስ አምስቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

3) የቦርዱ ውሳኔ የሚሰጠው በስብሰባዉ በተገኙ አባላት አብላጫ ድምጽ ሲደገፍ ይሆናል፤

4) ቦርዱ የራሱን የውስጥ አሰራር ስርዓት በተመለከተ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ሳይቃረን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፤

74. በቦርዱ ዉሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 71 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት በቦረዱ በሚሰጥ ዉሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታዉን በይገባኝ በ30 ቀናት ዉስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

75. በቦርዱ የሚመሩ አደረጃጀቶች

በዚህ አዋጅ የተቋቋሙት የጠበቆች ዲሲፕሊን ጉባኤ እና የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል፡፡

76. የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ

1) የጠበቆች ዲሲፕሊን ጉባኤ ከዚህ በኋላ “ጉባኤው” እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2) የጉባኤው አባላት ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ ናቸው፡-

ሀ) ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ሁለት ተወካይ፤

ለ) ከጠበቆች ማህበር ሁለት ተወካይ፤

ሐ) ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ተወካይ፡፡

3) የአንድ አባል የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን ከሁለት ግዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም

4) የጉባኤዉ ሰብሳቢ ከአባላቱ ዉስጥ በጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ የሚሰየም ይሆናል፤

5) ጉባኤዉ፡-

ሀ) እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸዉም ጊዜ መሰብሰብ ይችላል፤

ለ) ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፤

ሐ) ዉሳኔዎችን በድምጽ ብልጫ ያሳልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል ሲሆን በሰብሳቢዉ በኩል ያለዉ ድምጽ ዉሳኔ ሆኖ ይጸድቃል፤

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ከ(ሀ)-(ሐ) የተደነገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባኤዉ የራሱን የስብሰባ ስነ-ስርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

77. የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ ስልጣን እና ተግባራት ጉባኤዉ፡-

1) የጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የሥራ አፈጻጸም ከሙያ ሥነ ምግባር ደንብ ጋር የተጣጠመ መሆኑን መከታተል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

2) ይህንን አዋጅ ወይም የስነ-ምግባር ደንብ ወይም መመሪያ በመተላለፍ በጠበቃ ላይ የሚቀርብ ክስን ይመረምራል፤ ክሱ ጠበቃዉን የሚያስቀርብ መሆን አለመሆኑን ይወስናል፤

3) ክሱ እና ማስረጃዉ ጠበቃዉን የሚያስቀርብ መሆኑን ከወሰነ ጠበቃዉ መልሱን በ30 ቀናት ዉስጥ እንዲያቀርብ በመጥሪያ ላይ በመግለጽ ክሱን ለጠበቃዉ ይልካል፤

4) በጠበቃዉ ላይ የቀረበዉን ክስ እና ማስረጃ፤ እንዲሁም በጠበቃዉ በኩል የተሰጠ መልስ እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ዉሳኔ ይሰጣል፤

5) የጠበቆች ስነ-ምግባር ብቃት የሚጎለብትበትን፤የጥብቅና ሙያ ክብር የሚጠበቅበትን ሁኔታ እያጠና ለቦርዱ ሀሳብ ያቀርባል፤

78. የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ

1) የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ ከዚህ በኋላ “የፈተና ኮሚቴ” እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2) የኮሚቴው አባላት ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ ናቸው፡-

ሀ) ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ሁለት ተወካዮች፤

ለ) ከጠበቆች ማህበር ሁለት ተወካይ፤

ሐ) ከፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንድ ተወካይ፤

መ) ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ህግ ትምህርት ቤት አንድ ተወካይ፤

3)የአንድ አባል የስራ ዘመን ሁለት አመት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ ለመረጥ አይችልም፡፡

4) የኮሚቴዉ ሰብሳቢ በጠበቆች ማህበር የሚመረጥ ይሆናል፤

5) የፈተና ኮሚቴዉን ስብሰባ በተመለከተ፡-

ሀ) ኮሚቴዉ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ ሊሰብሰብ ይችላል፤

ለ) ከኮሚቴዉ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፤

ሐ) የኮሚቴዉ ዉሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ የሰብሳቢው ድምጽ ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡

79. የፈተና ኮሚቴው ስልጣን እና ተግባራት፡-

የፈተና ኮሚቴዉ፡-
1) በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የጥብቅና ፍቃድ ከሚሰጠው የስራ ክፍል ጋር በመመካከር ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የጥብቅና ችሎታ መመዘኛ ፈተና እያዘጋጀ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ ለአመልካቾች ይሰጣል፤

2) የፈተና ወረቀቶችን ያርማል፤ ለማለፊያ የሚያበቃ ነጥብ ይወስናል፤ ዉጤቱን በይፋ ያስታዉቃል፤

3) የፈተና ስነ-ስርአት ደንብ አዘጋጅቶ ለቦርዱ አቅርቦ ሲጸድቅ በስራ ላይ ያዉላል፡፡

ንዑስ ክፍል ሶስት

በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ስለሚመራ አደረጃጀት

80. የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ስልጣን እና ተግባር

ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፡-

1) የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ የሚያቀርብለትን የዉሳኔ ሀሳብ
በመመርመር የጥብቅና ፍቃድ ይሰጣል ወይም ይከለክላል፤

2) የጥብቅና ፍቃድ፤ የጥብቅና ድርጅቶችን፤ እና ከጠበቃ እና ጥብቅና ድርጅቶች ጋር የሚሰሩ ሰዎችን ይመዘግባል፣ የጥብቅና ፍቃድ ያድሳል፣

3) የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ በሚወስነዉ መሰረት የጥብቅና ፍቃድ ያግዳል፣ ይሰርዛል፡፡

4) በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሰረት ለሚሰጠው የጥብቅና ፍቃድና ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያ ይሰበስባል፡፡

5) በጠበቆችና በጥብቅና ድርጅቶች ለሚሰጡ የሕግ አገልግሎቶች መለኪያዎችን ያወጣል፤

6) በፌዴራል እና በክልል ያሉ የጥብቅና ሙያ አስተዳደደር ሥርዓቶች የተጣጣሙ እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋል፤

7) የስነ ምግባር ጥሰት ፈጽሟል ተብሎ ጥቆማ በቀረበበት ማንኛውም ጠበቃ ላይ የስነ-ምግባር ጥሰቱ ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ ምርመራ ያካሂዳል፣ የዲስፕሊን ክስ ይመሰርታል፤

8) ሌሎች በዚህ አዋጅ፤ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸዉ ህጎች የተሰጡትን ስልጣን እና ተግባራት ይፈጽማል፡፡

9) በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በሙሉ ወይም በከፊል ለጠበቆች ማህበር በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

81. የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 82 ስር የተዘረዘሩት ስልጣን እና ተግባራት ያሉት የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ይቋቋማል፤

2) ኮሚቴዉ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ሁለት ተወካዮች፤

ለ) ከጠበቆች ማህበር ሁለት ተወካዮች፤ እና

ሐ) ከፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት አንድ ተወካይ፡፡

3) የአንድ አባል የስራ ዘመን ሁለት አመት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፡፡

4) የኮሚቴዉ ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ የሚሰየም ይሆናል፡፡

82. የኮሚቴዉ ስልጣን እና ተግባር

ኮሚቴው፡-

1) የአመልካቹን ማስረጃዎች መርምሮ አመልካቹ ፍቃድ እንዲሰጠዉ ወይም አንዳይሰጠዉ ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የዉሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤

2) አመልካቹ ለፍትህ ስራ አካሄድ የሚስማማ የስነ-ምግባር ብቃት ያለዉ መሆኑን ለማረጋገጥ ማንኛዉንም ሰዉ መጠየቅ ወይም ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር ይችላል፡፡

83. የኮሚቴዉ ስብሰባ

1) ኮሚቴዉ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸዉም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

2) ከኮሚቴዉ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

3) የኮሚቴዉ ውሳኔዎች በስብሰባዉ በተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢዉ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴዉ የራሱን የስብሰባ ስነስርአት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

ክፍል ስድስት

የዲሲፕሊን ጥፋቶች እና ቅጣት

84. ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት

የሚከተሉትና መሰል በጠበቆች ስነ-ምግባር ደንብ የሚጠቀሱ በጠቢቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚፈፀሙ ጥፋቶች ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸዉ፡-

1) የጥብቅና ፍቃድን ለደንበኛ፤ለፍርድ ቤት ወይም ለሚመለከተዉ አካል እንዲያሳይ በተጠየቀ ጊዜ ለማየሳት ፈቃደኛ ያለመሆን፤ 2) ጉዳዩ ያለበትን ሁኔታና የደረሰበትን ደረጃ በደንበኛው ሲጠየቅ በአግባቡ ያለማሳወቅ፣ ደንበኛን ማመናጨቅ ወይም ክብሩን መንካት፤
3) ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት በቀጠሮ ቀን ፍርድ ቤት በሰዓቱ ያለመገኘት ወይም መዘግየት ወይም ያለበቂ ምክንያት ደንበኛን ብቻ ፍርድ ቤት በመላክ መቅረት፤ 4) ለጠበቆች ማህበር መክፈል የሚጠበቅበትን ክፍያ ወይም መዋጮ በተደጋጋሚ እና በወቅቱ ያለመክፈል፤ 5) የጥብቅና ፍቃድን በወቅቱ አለማሳደስ፤

85. የቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ቅጣት 1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የቃል ማስጠንቀቂያ በዲሲፕሊን ጉባኤው ይሰጠዋል፡፡ ለሁለት ጊዜ የቃል ማስጠንቀቂያ የተሰጠዉ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለሶስተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ጥፋት ከፈጸመ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡ 2) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተጠቀሱትን ጥፋቶች የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡ 3) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 84 (5) የተጠቀሰውን ጥፋት የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደነገሩ ሁኔታ ከብር አምስት ሽ እስከ ብር ሰባት ሽ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

86. ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት

የሚከተሉት እና መሰል በጠበቆች ስነ-ምግባር ደንብ የሚጠቀሱ በጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚፈፀሙ ጥፋቶች ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸዉ፡-

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18(3) ስር የተዘረዘሩ ሰዎችን በጠበቃ ረዳትነት ወይም በህግ ጉዳይ ጸሀፊነት መቅጠር እና ማሰራት፤

2) በስሩ የቀጠራቸውን የጠበቃ ረዳትና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ለፍቃድ ሰጭው አካል ያለማሳወቅና ያለማስመዝገብ፤

3) ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት ተለዋጭ ቀጠሮ በተደጋጋሚ መጠየቅና የፍ/ቤት ጉዳይ እንዲጓተት ማድረግ፤

4) የጥብቅና አገልግሎት መስጫ ቢሮ ሳይኖር የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤

5) በህግ ከተፈቀደው ምክንያት ውጭ ተከታታይ የግዴታ የህግ ስልጠና በአግባቡ አለመውሰድና፤

6) የደንበኛን ሚስጥር አለመጠበቅ፤ 7) ነፃ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጥ በሚመለከተዉ አካል ሲመራለት ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን፤
8) የጥብቅና ስራን በደላላ አማካኝነት መስራት ወይም ለሌሎች ጠበቆች የድለላ ስራ መስራት፤

9) ከደንበኛ ጋር የሚደረግ የጥብቅና አገልግሎት ውል ስምምነትን በፅሁፍ ያለማድረግ እና በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ አለማስመዝገብ ፤

10) ያለበቂ ምክንያት የጥብቅና ውልን ማቋረጥ ወይም በጥብቅና ውሉ ከተገለፀው የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ በተጨማሪ ከደንበኛው አላግባብ ተጨማሪ ክፍያ መጠየቅና መቀበል፤ 11) የመድን ዋስትና ሳይገባ ወይም የመድን ዋስትናው በወቅቱ ሳይታደስ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤ 12) የጥብቅና ፍቃዱን ለጥብቅና ፍቃድ ሰጭው ተቋም ሳይመልስ በሌላ ቋሚ ስራ ተሰማርቶ መገኘት፤ 13) የጥቅም ግጭት የሚያስነሳ ወይም ያለበት ጉዳይ መሆኑን እያወቀ ጉዳዩን መያዝ፤

14) ከተሰጠው የጥብቅና ፍቃድ ደረጃ በላይ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤

15) የደንበኛውን ማስረጃ በአግባቡ ለፍርድ ቤት አለማቅረብና ከአቅም በታች በመከራከር መዝገቡ ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፤

16) የጥብቅና ፍቃድን በማንኛውም ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን መጠቀሚያ አሳልፎ መስጠት፤

17) ነፃ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታውን እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በአግባቡ ባለመወጣት የደንበኛን ጉዳይ እንዲበላሽ ወይም ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ

18) ከተቃራኒ ባለጉዳይ ጠበቃ ጋር በመመሳጠር ወይም ማስረጃ በማጥፋት የደንበኛ ጉዳይ ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፤

19) የህግ መሰረት የሌለውንና እንደማያዋጣ በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ ያዋጣል በማለት መያዝና ከደንበኛ ክፍያ መቀበል፤

20) ሐሰኛ ማስረጃ በመጠቀም ወይም በማንኛውም ሁኔታ በማታለል የጥብቅና ፍቃድ ማውጣት፤

21) በእምነት ማጉደል፣ ማታለል፣ ማጭበርበር፣ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት ወይም መገልገል፣ስርቆት፣ እና በመሳሰሉት ከስነ ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣት፤
22) ሐሰተኛ ማስረጃ ማቅረብ ወይም እንዲቀርብ ማድረግ፣ ሀሰተኛ ምስክር በማዘጋጀት በሀሰት ማስመስከር፣ተከሳሽ ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ ወይም እንዲጠፋ ማድረግ ወይም መምከር፣ ለተቃራኒ ወገን ጠቃሚ የሆነን ማስረጃ እንዳይጠቀምበት በማሰብ ማጥፋትና ፍትህ እንዲዛባ ማድረግ፤ 23) በታገደ ወይም በተሰረዘ የጥብቅና ፍቃድ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤

87. የከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ቅጣት 1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 84 ከንዑስ አንቀጽ (3) - (7) ባሉ ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ፤ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 ከንዑስ አንቀጽ (1) – (7) ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ከብር ሰባት ሽ አምስት መቶ እስከ ብር አስራ አምስት ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ 2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 ከንዑስ አንቀጽ (8)-(13) ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ከብር ሃያ ሽ እስከ ብር ሰላሳ ሽ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 ከንዑስ አንቀጽ (14)-(19) ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደነገሩ ሁኔታ እስከ ስድስት ወር ለሚደርስ ጊዜ የጥብቅና ፈቃዱ ይታገዳል፡፡ 4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 ከንዑስ አንቀጽ (20)-(23) ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፍቃዱ ይሰረዝበታል፡፡ 5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተጠቀሱትን ቅጣቶች በአምስት አመት ጊዜ ዉስጥ ለሁለት ጊዜ የተቀጣ ጠበቃ ሌላ ተመሳሳይ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ ፍቃዱ ከ6 ወር እስከ 1 አመት ለሚደርስ ጊዜ ሊታገድ ይችላል፡፡ 6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 ስር የተጠቀሰዉን ቅጣት ለሁለት ጊዜ የተቀጣ ጠበቃ ወይም የትብቅና ድርጅት ሌላ ተመሳሳይ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ የጥብቅና ፍቃዱ የሚሰረዝ ይሆናል፡፡ 7. በዲሲፕሊን ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና መቀጣት በወንጀል የሚያስጠይቁ የዲሲፕሊን ጥፋቶችን በተመለከተ የወንጀል ተጠያቂነትን አያስቀርም፡፡

88. ስለዲሲፕሊን ክስ አቀራረብና ይርጋ

1) የዲስፕሊን ክስ አቀራረብ እና የክርክር ስነስርአት ቦርዱ በሚያወጣዉ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡ 2) በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ የሚቀርብ ክስ የዲሲፕሊን ጥፋቱ በተፈፀመ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡ 3) በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ የሚቀርብ ክስ የዲሲፕሊን ጥፋቱ በተፈፀመ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

89. ይግባኝ
1) በዲሲፕሊን ጉባኤው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን የዲሲፕሊን ጉባኤው ውሳኔ ግልባጭ በደረሰዉ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ 2) የይግባኝ ክርክር ሂደት በመደበኛው የወንጀል ይግባኝ አቀራረብ ስርዓት መካሄድ

አለበት፡፡ 3) በቦርዱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን የህግ ስህተት አለ ብሎ ካመነ የቦርዱ የውሳኔ ግልባጭ በደረሰው በሰላሳ ቀናት ወስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

90. የወንጀል ቅጣት

በዚህ አዋጅ በወንጀል የሚያስቀጡ ጥፋቶችን የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት አግባብ ባለዉ የወንጀል ህግ ይቀጣል፡፡

91. ስለመሰየም

1) በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት የተቀጣ ጠበቃ የጥፋተኛነት ሪከርድ እንዲሰረዝለትና ስሙ እንዲመለስለት መጠየቅ ይችላል፡፡ 2) የመሰየም አቤቱታ የሚቀርበው ለዲሲፕሊን ጉባኤ ሆኖ አቤቱታው ሊቀርብ የሚችለው የጥፋተኛነት ውሣኔ ከተሰጠ ከሁለት ዓመት በኋላ ነው፡፡ 92. የመሰየም ሥርዓት

1) አመልካች ጠበቃ የመሰየም አቤቱታውን ለዲሲፕሊን ጉባኤው ያቀርባል፡ 2) የዲሲፕሊን ጉባኤውም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ወይም ሌላ

የሚመለከተው አካል በአቤቱታው ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡ 3) የዲሲፕሊን ጉባኤውም የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ወይም የሚመለከተውን አካል አስተያየት ከተቀበለና አመልካቹን በአካል በማነጋገር አስፈላጊውን ምርመራ ካደረገ በኋላ ጥፋቱ ከሪከርድ እንዲሰረዝ ይወስናል፡፡ 93. የመሰየም ውጤቶች

1) አመልካቹ ጠበቃ የጥፋተኛነት ሪከርድ ይሰረዝለታል፤ 2) ሪከርዱ በማናቸውም አይነት ውሣኔ ላይ አይጠቀስም፤ ፍቃዱ ተሰርዞበት ከሆነ ለደረጃዉ የሚሰጠዉን ፈተና ተፈትኖ ካለፈ እና በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ፍቃዱ ይመለስለታል፡፡ 3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 (20)- (23) ስር በተደነገጉት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ምክንያት የጥብቅና ፍቃዱ የተሰረዘበት ወይም በእነዚሁ ድርጊቶች በወንጀል የተቀጣ፤ ወይም ከሚሰጠው የጥብቅና አገልግሎት ጋር በተያያዘ በሙስና ወንጀል የተቀጣ፤ ወይም ታስቦ በሚፈጸም እና ከአስር ዓመት ጽኑ እስራት በላይ በሚያስቀጣ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የተሰየመ ቢሆንም የጥብቅና ፍቃዱ አይመለስለትም፣ በጥብቅና አገልግሎት ሙያ ድጋሚ መሰማራት አይችልም፡፡ 94. ጉባኤው ስለሚሰጣቸው ትዕዛዞች
የዲሲፕሊን ጉባኤው አንድ ጠበቃ እንዲሰየም ሲወስን ጠበቃው ጉባኤው ለሚወስነው ጊዜ ያህል ነፃ የማህበረሰብ አግልገሎት እንዲሁም ጉበኤው ለሚወስናቸው ጉዳዮች መጠን ያህል ነፃ የሕግ አገልግሎት እንዲሰጥ ሊያዝ ይችላል፡፡

95. ተፈፃሚነት መሰየምን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ለተቀጡ ጠበቆችም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

96. መሰየምና ቀላል ጥፋቶች በቀላል ጥፋት የተቀጣ ጠበቃ የመሰየም አቤቱታ ማቅረብ ሳያስፈልገው ከሶስት ዓመት በኋላ ሪከርዱ ይሰረዝለታል ወይም ቀሪ ይደረግለታል

ክፍል ስምንት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

97. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤

2) ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፤ ቦረዱ እና ማህበሩ በዚህ አዋጅ የተሰጣቸዉን ስልጣን እና ተግባራት ለማስፈጸም የሚያስችላቸውን መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

98. መሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1) በዚህ አዋጅ መሠረት ቦርዱ እና ማህበሩ ሀላፊነታቸዉን እስኪረከቡ ድረስ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በነባር ሕጎች መሠረት የጥበቅና አስተዳደር ስራን ይቀጥላል፤

2) ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች ይህ ሕግ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ጸንተው በነበሩት ህጎች መሠረት ውሣኔ ያገኛሉ፡፡

99. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕግጋት

1) የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፍቃድ እና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/2000 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

2) ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ስርዓት በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

100. ተፈፃሚነታቸው ስለሚቀጥል ሕጎች በፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች ምዝገባና ፍቃድ አሰጣጥ አዋጅ ቁጥር 199/2000 መሰረት የወጡ ደንብ እና መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

101. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል

አዲስ አበባ ቀን 2012 ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት